# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ታህሳሥ 7/2003

## ኢሕአፓ ዳግም ለትግል ተነሱ ማሰታወቂያዎችን በአዲስ አበባ ለጠፈ

ቅዳሜ ታህሳሥ 2 ቀን የኢሕአፓ ቢጫ ፀረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም የሚል መልዕከት አዘል መፈክርን የያዙ ማስታወቂያዎች በአዲስ አበባ የስልክ እንጨቶች፤ የፖስታና ቴሌ ግድግዳዎች፤ማሰታወቂያ መለጠፊያ ዎች፤ መኪናዎች ወዘተ ተለጥፈው ለወያኔ አገዛዝ ዳግም ድንጋጤንና ጭንቀትን አከናንበዋል።

የልጠፋው ስራ የተከናወነው በሚቀጥሉት አካባቢዎች ነው፤

-- ፒያሳ

-- ጉለሌ

-- 4/5/6 ኪሎዎች

-- ፈረንሳይና ቤላ

-- መርካቶ

--- መገናኛ

--- ከመሿለኪያ መንገድ እስከ ሳሪስ ሀያ ሁለት

ማስታወቂያዎቹ በተለጠፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የወያኔ የፀጥታ ሰራተኞች ለመቅደድ ቢሞክሩም በአጠቃላይ ከየቦታው ለማንሳት ቀናት ፈጅቶባቸዋል። ኢሕአፓ ይህን የማስታወቂያና የቅስቀሳ እንቅስቃሴ እያደረገ ያለው ከሕዘብ መሀልና ጎን በመገኘት ትግሉን ለማጠናከር እየጣረ መሆኑን ለማብሰርና ለሚፋፋም ትግልም ሕዝብን ለመጥራት መሆኑ ግልፅ ነው። የወያኔ የፀጥታ መዋቅር የኢሕአፓን የቅስቀሳ እንቅስቃሴ ለማፈን (ፍኖተ ራዲዮንን ማገድ ወዘተ) ልዩ ልዩ እርምጃዎችን ቢወስድም ኢሕአፓ በፈለገ ጊዜና ቦታ የቅስቀሳ እርምጃ ሊወሰድ መቻሉን ማሳየቱ የዚህ ዘረኛ ቡድን ድንፋታ ባዶና መሰረተቢስ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ኢሕአፓ ራሱን ከጥቃት እየጠበቀ የመለስን ጨቋኝ አገዛዝ የሚያጋልጥና የሚጎዳ እንቅስቃሴውን እያፋፋመ ይቀጥላል።

እናቸንፋለን!!







EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC 20056
USA
Tel 202-291-4217 Fax 202-291-7645

e-mail: espic@aol.com
website: EPRP.com

EPRP
B.P.22
Bois Colombes 922270
France